MONTGOMERY COUNTY MARYLAND 1776 GARDEZ BIEN

ABS
ALCOHOL BEVERAGE SERVICES

# ሞንትጎመሪ ካውንቲ
# የአልኮል መጠጥ አገልግሎቶች

## የፈቃድ፣የደንብ እና የትምህርት ክፍል

## ALERT

የአልኮል ሕግ አፈጻጸም እና ቁጥጥር ስልጣና

# ማስታወሻዎች

- ✓ አሰልጣኞችዎን ይተዋወቁ
- ✓ በአስተያየት መሰብሰቢያ ውስጥ ይሳተፉ
- ✓ የአልኮል መሰረታዊ እውነታዎች አስተያየት መሰበሰቢያ
- ✓ የስራ ድርሻ አስተያየት መሰብሰቢያ



# በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ይከታተሉን



Facebook: @MoCoRASP

X: @MoCo_RASP

Instagram: @MoCoRASP

# ማስታወቂያዎች







- ከፈቃድ ፣ ደንብ እና ትምህርት ክፍል (LRE) ቢሮዎች፡-
  - እርስዎ የሚገኙበትን የአድራሻ መረጃ ትክክለኛነት ያረጋግጡ (ማለትም ስልክ ቁጥሮች፣ ኢሜይሎች እና የፖስታ አድራሻዎች)።
- የተሳትፎ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፡-
  - በስልጠናው መጨረሻ ላይ ሊንክ (link) እንሰጥዎታለን። የተሳትፎ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለማግኘት መረጃውን መሙላት ያስፈልግዎታል።






# አጀንዳ

- ክፍል 1፤ የአልኮል ሕግ አፈጻጸም እና ቁጥጥር ስልጠና (ALERT) አስፈላጊነት እና ስለእኛ ማንነት
- ክፍል 2 ፤ አልኮል በሰውነት ላይ ያለው ተጽእኖ
- ክፍል 3 ፤ ኃላፊነቱን የሚወጣ የአልኮል መጠጥ አገልግሎት
- ክፍል 4 ፤ የሜሪላንድ የአልኮል ህጎች እና ደንቦች
- ክፍል 5 ፤ ኢንስፔክሽኖች
- ክፍል 6 ፤ ከ 21 ዓመት በታች አልኮል መጠቀም እና መታወቂያዎች
- ክፍል 7 ፤ የስልጠና ምዘና እና ለተወሰኑ ተሳታፊዎች መሰናበቻ / መዝጊያ
- ክፍል 8 ፤ የፍቃድ ኮሚሽን ቢሮ (BLC) ችሎት አሰራር የግንዛቤ ስልጠና





# ክፍል 1

የአልኮል ሕግ አፈጻጸም እና ቁጥጥር ስልጠና (ALERT) አስፈላጊነት እና ስለኛ ማንነት

- በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ 86% የሚሆኑ አዋቂዎች በሕይወት ዘመናቸው ውስጥ በአንድ ወቅት አልኮል ይጠጣሉ።
- በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በየዓመቱ 95,000 ከአልኮል ጋር የተያያዘ ሞት አለ
- 30% የሚሆኑት ከማሽከርከር ጋር የተያያዙ የሕይወት መጥፋቶች ጠጥቶ ከማሽከርከር ጋር የተያያዙ ናቸው።
- ከ10 ታዳጊ ወጣቶች 4ቱ (ከ12-20 አመት እድሜ ያላቸው) በህይወታቸው ቢያንስ 1 መጠጥ እንደጠጡ ይናገራሉ።
  - በበጀት አመት (FY) 22-23 ህግ የማክበር ሬት (Rate) ፣ **62.7 %**
- በበጀት አመት (FY) 21-22፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ **1,713** ከአልኮል ጋር የተገናኙ እስራቶች ነበሩ። በዝርዝር ሲቀመጥ:-
- ○ በዓመት ውስጥ በየቀኑከ 4 በላይ ሰዎች አልኮል ጠጥተው ሲነዱ በቁጥጥር ስር ውለዋል።

የመረጃ መንጮች :- NIAAA፣ የዋሽንግተን አካባቢያዊ የአልኮል ፕሮግራም (WRAP)፣ 2020 መንገዶቻችን ምን ያህል ደህንነታቸው የተጠበቀ ነው በሚል የተዘጋጀ ሪፖርት ፣ የሜሪላድ የጤና ቢሮ www.wrap.org



# የአልኮል መጠጥ አገልግሎቶች(ABS)


- በሞንትጎመሪ ካውንቲ  ከ1000 በላይ የሚሆኑ የንግድ ተቋማት የአልኮል ንግድ ፍቃድ አሰጣጥን ፣አፈጻጸምን እና የግንዛቤ ትምህርትን ያከናውናል።
- በሞንትጎመሪ ካውንቲ ላሉ የንግድ ተቋማት የአልኮል መጠጥ በጅምላ እና በችርቻሮ ያከፋፍላል ፣ በተጨማሪም በአብዛኛው ጊዜ ወይን እና ቢራ በጅምላ ያከፋፍላል
- የተገኘው ገቢ ወደ ካውንቲው አጠቃላይ ፈንድ ይገባል ፤ በዓመት ከ 30 ሚሊዮን ዶላር በላይ



# የአልኮል እና መጠጦች አገልግሎት (ABS) ዋና ዋና ተግባራት

- **የሞንትጎመሪ ካውንቲ የፍቃድ ኮሚሽነሮች ቦርድ፣** ለአልኮል መጠጦች የሽያጭ ፈቃዶችን ይሰጣል ፣ ይሰርዛል ወይም ያግዳል እና ለህግ ጥሰቶችን ቅጣቶች ይሰጣል።
- **የማህበረሰብ ተደራሽነት ፕሮግራሞች፣** የስልጠናዎች እና የደህንነት ጥምረት/ትብብሮች ፣ የንግድ ሊጎች እና የማህበረሰብ ስብሰባዎች
- **የችርቻሮ መደብሮች፣**
    - 27 መደብሮች
    - ቢራ ፣ ወይን እና የአልኮል መጠጦች
    - ለማሕበረሰቡ እና ለንግድ ተቋማት ግዢዎች








# ክፍል 2

አልኮሆል በሰውነት ላይ ያለው ተጽእኖ

# አልኮል ምንድን ነው?

- በቢራ፣ በወይን እና በአልኮል መጠጥ ውስጥ ያለው ዋናው ንጥረ ነገር
- ስካርን ያስከትላል
- እንቅስቃሴን የሚገድብ ፣ ማዕከላዊውን የነርቭ እንቅስቃሴ ይቀንሳል?











https://www.youtube.com/watch?v=I_OoW_w-uM8

# የመጠጥ መጠኖች



12 oz ቢራ
5% የአልኮል መጠን (ABV)

=



5 oz ወይን
12% የአልኮል መጠን (ABV)

=



1 oz መጠጥ
50% የአልኮል መጠን (ABV)

=

**½ oz የአልኮል መጠን በቻ**

**ሁሉም ኤቲል (Ethyl) አልኮሆል ናቸው!**

# አልኮሆል በሰውነታችን ውስጥ የሚሰራበትን መጠን የሚወስኑ ምክንያቶች

1. የሰውነት መጠን (ጾታ)
2. ስሜት / ጭንቀት
3. ጥንካሬ እና የመጠጥ አይነት
4. አመጋገብ
5. ሕክምና እና መድሃኒቶች
6. መጠጥ የሚወሰድበት ፍጥነት መጠን
7. ዕድሜ









# ደም ውስጥ ያለ የአልኮል መጠን (BAC)

- **ደም ውስጥ ያለ የአልኮል መጠን (BAC)፣** በአንድ ሰው ደም ውስጥ ያለው የአልኮል መጠን በመቶኛ
- **በሜሪላንድ ወስጥ አልኮል ጠጥቶ ማሽከርከር፣.08 BAC ፡-በሜሪላንድ** ውስጥ በጣም ከባድ የሆነ ወንጀል ሲሆን እስራት እና የወንጀል መዝገብ ጋር የተያያዘ መዘዝ ያስከትላል።



# የስካር ጤቶች በቅደም ተከተል

1. ከፍተኛ የደስታ ስሜት(Euphoria)
2. የጋለ  ወይም የመነቃቃት ስሜት
3. ግራ መጋባት
4. የንቃተ ህሊና ማጣት/ድንዛዜ(stupor)
5. እራስን መሳት ወይንም ኮማ(coma) ውስጥ መግባት
6. ሞት





# ክፍል 3

ኃላፊነቱን የሚወጣ የአልኮል መጠጥ አገልግሎት

# ኃላፊነት ያለው የመጠጥ አገልግሎት

- አልኮልን የሚሸጡ እና የሚያቀርቡ በኃላፊነት ለማገልገል እንዲችሉ ዕውቀት እና ክህሎት ያላቸው እና የሚሪላንድ አልኮል አገልግሎት ህጋዊ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን **ያረጋግጣል።**

- ከመጠን በላይ አልኮል እንዳይጠጣ እና ከመጠን በላይ በመጠጣት የሚከሰቱትን ጉዳቶችን ለመቀነስ **ለአስተናጋጆች ድጋፍ ይሰጣል**



# ተስፋ ሰጪ የአሰራር ለምዶች

የእርስዎ የንግድ ተቋም

የምግብ ዝርዝር (ሜኑ)

ሰራተኞች



# የእርስዎ የንግድ ተቋም

- «ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተግባቢ» የእርስዎ ብራንድ አካል በማድረግ **ተግባራዎ ያድርጉ**
- ከመጠን በላይ መጠጣትን የሚያበረታቱ ማስተዋወቂያዎችን **ያስወግዱ**
- በሚታዩ ቦታዎች የአልኮል ፖሊሲዎችን **ይለጥፉ**
- ተለዋጭ መጓጓዣ አገልግሎት **ያዘጋጁ**
- መታወቂያ መጠየቂያ ፖሊሲዎችን **ያዘጋጁ** እና በቋሚነት ይተግበሩ
- የአስተናጋጅ ዕድሜን በተመለከተ ያሉ ህጎችን **ያክብሩ**
- በሰነድ አያያዝ ዙሪያ ያሉ ፖሊሲዎች ተግባራዊነታቸውን **ያረጋግጡ**



# የምግብ ዝርዝር (ሜኑ)

- **ደረጃውን የጠበቀ** የመጠጥ አዘገጃጀት ይከተሉ ብሎም ትክክለኛዎቹን መሳሪያዎች ይጠቀሙ ፤ ነፃ መጠጥ መቅዳትን ያስወግዱ
- በሚሸጡት መጠጥ ላይ የአልኮል መጠን በመቶኛ (ABV percentaage) **ያሳዩ**
- ድንበኞች በራቸው የሚጠቀሙባቸው ኪወስኮችን (self serving kiosks) **ይቆጣጠሩ**
- የአልኮል መጠጦች በሚቀርቡበት ጊዜ ሁሉ ከአልኮል ነጻ የሆኑ መጠጦች በቀላሉ እንዲገኙ **ያድርጉ**
- ውሃ እና ነፃ ምግብ **ያቅርቡ**



# ሰራተኞች

- ሰራተኞችን **ማሰልጠን** ፤ ለአልኮል ደህንነትን ቅድሚያ መስጠት:-
  - መታወቂያዎችን እንዴት እንደሚጠይቁ/እንደሚያረጋግጡ፣ አንድ ደንበኛ ተጨማሪ እንዳይጠጣ እንዴት እንደሚያስቆሙ እና አገልግሎትን እንዴት መከልከል እንደሚችሉ ያስተምሯቸው
  - የስካር ምልክቶችን ይወቁ
  - የሚቀርቡትን መጠጦች የአልኮል መጠን (ABV) ይወቁ
  - መጠጦች የት እንደሚሄዱ ይወቁ
  - የሚሰጡትን የመጠጥ ብዛቶች ይከታተሉ
- ሰራተኞች የአልኮል የግንዛቤ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ እድል **ይስጡ**
- ሰራተኞች በሚሰሩበት ጊዜ የአልኮል መጠጦችን አለመጠጣታቸውን **ያረጋግጡ**



# የሲቪል ተጠያቂነት እና ግዴታቸውን ለመወጣት የሚያደርጉት ምክንያታዊ ጥረት



**ሕጉ እንዲወሰዱ የሚጠይቃቸው እርምጃዎች፡-**

- ስካርን ለመከላከል እርምጃዎችን መውሰድ
- የሰከሩ ሰዎች ጉዳት እንዳያደረሱ መከላከል

**ይህ ህገወጥ ነው፡-**

- ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች አልኮል መሸጥ፣ መያዝ ወይም መጠጣት
- ለሰከረ ሰው አልኮል መሸጥ ወይም መስጠት


**እንደ መጠጥ ቤት አስተናጋጅ ወይም አልኮል ሻጭ ለሚወስኑት ውሳኔ እንደ ግለሰብ ሊከሰሱ ይችላሉ።**



# የአልኮል ቦርድ ጥሰቶች

**ሕጉ እንዲወሰዱ የሚጠይቃቸው እርምጃዎች፡-**

- ፍርድ ቤቶች ጉዳዮችን የሚፈቱበት መንገድ ፣ የፍቃድ ኮሚሽነሮች ቢሮ (BLC) አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡-
  - ከቦርድ ውሳኔ በኋላ በ 60 ቀን ውስጥ በአልኮል ሕግ አፈጻጸም እና ቁጥጥር ስልጠና (ALERT) ውስጥ መሳተፍ
  - ቅጣት የመጣል ሂደትን ማስተዳደር/መቆጣጠር
  - የፍቃድ እገዳ እና መሻር





# አገልግሎትን ለመከልከል የሚረዱ ምክሮች



አካባቢዎን ይቃኙ እና ወደ ስካር የሚያመሩ እንግዶችን ያስተውሉ።

ወደ ማንኛውንም የሰከረ ደንበኛ ጋር ከመቅረብዎ በፊት፣ ከማኔጀርዎ እና ከሴኩሪቲ ሰራተኞች ፈቃድ እና እርዳታ ይጠይቁ።

ከአሁን በኋላ አልኮልን መስጠት እንደማይችሉ በቆራጥነት ነገር ግን በትህትና ለደንበኛው ያሳውቁ።

"እኔ የሚሉ አነጋገሮችን " ይጠቀሙ እናም በፈራጅነት መንገድ አያናግሩ።

በምትኩ አልኮል ያልሆነ መጠጥ ይፈልጉ እንደሆነ ይጠይቋቸው።

ለደንበኛ መጠጥ ላለመከልከል ብለው አልኮሎችን በጭራሽ በውሃ እንዳይቀላቅሉ።

መረጃ ፡፡ የተከሰቱ አደጋዎችን ጽፈው ያስቀምጡ።

ወደ ቤት እንዲያደርሱዋቸው ለጓደኛቸው ወይም ወደ ታክሲ ይደውሉ።

ግለሰቡ ለደህንነት የሚያሰጋ ነገር ለማድረግ የሚያስፈራራ ከሆነ ለፖሊስ ለመደወል አያመንቱ።




# ክፍል 4

የአልኮል ህጎች እና መመሪያዎች

# የንግ ስራ ፍቃዶች(licenses) ፣ በሰነድ የተረጋገጡ ፍቃድዎች(Permits) እና ፈቃዶች(permissions)

- 34ቱ የፍቃድ ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፣
  - ቢራ፣ ወይን እና አልኮል (ሊከር)
  - በንግድ ተቋሙ ውስጥ እና ከተቋሙ ውጪ
  - ለሆቴሎች ልዩ ፍቃዶች፣ የኪነጥበብ/ሥነ ጥበብ ጋለሪዎች፣ የድርጅት ስልጠና፣ የምግብ ዝግጅት ትምህርት ቤቶች
  - ፌስቲቫሎች እና የአንድ ቀን ቃዶች
- የሚከተሉትን ጨምሮ የተለያዩ ቃዶች
  - የምግብ አቅርቦት
  - የቢራ እና የወይን ቅምሻ
  - የወይን ኮርኬጅ (corkage)
  - የሚሞላ የቢራ መያዣ
  - የውጪ መቀመጫ ያለው ካፌ
  - የንግድ ተቋም እና ጊዜያዊ ማሻሻያ
  - ምግብ ለማብሰል አልኮልን መጠቀም









[የፍቃድ ዓይነቶች]

# በተለያዩ ምሳሌዎች (Scenario) ላይ ውይይት



- **ምሳሌ 1** ፣ አንዲት ወጣት ሴት ገብታ ወይን አዘዘች። መታወቂያዋን ስጠይቃት የቁም (Vertical) ቅርጽ ያለውን መታወቅያ ሰጠችኝ። አገልግሎት መስጠት አለብኝ?
  - እንደ ሁኔታው ይወሰናል! የቁም (vertical) ቅርጽ ያለው መታወቅያ መቀበል ሕገወጥ አይደለም፣ ነገር ግን ጥንቃቄ መደረግ አለበት።
- **ምሳሌ 2** ፣ እኔ XYZ ባር ውስጥ ቢራ እየጠጣሁ ጓደኛዬን እየጠበኩ ነው። ጓደኛዬ ደውላ ከመንገዱ ማዶ ያለው ABC ሬስቶራንት ውስጥ እየጠበኩህ ነው አለችኝ። እሷን ABC ሬስቶራንት ውስጥ ለማግኘት ቢራዬን ይዤ መንገዱን አቋርጬ በመሄድ ከእርሷ ጋር ተቀመጥኩ። ይህ ችግር አለው?
  - 3 ችግሮች፣ ክፍት ኮንቴይነር/መያዣ ፣ ያልተፈቀደ የአልኮል አይነት እና አካባቢው ላይ ለመጠቀም ያልተፈቀደ መጠጥ።
- **ምሳሌ 3** ፣ አንድ ወጣት ተቀመጠ እና ቢራ አዘዘ። ቢራውን ይዤ ስመለስ መታወቂያውን ለማየት በመጠየቅ ሳጣራው ከ 21 አመት በታች መሆኑን አረጋገጥኩ። ቢራውን በእጄ እንደያዝኩት ነው ። ምን አይነት ስህተት?
  - መታወቅያ ሳይጠየቅ እና ስይረጋገጥ መጠጥ መስጠት የሚለው ስህተት አልተፈጸመም ማለት ነው።

# በተለያዩ ምሳሌዎች (Scenario) ላይ ውይይት



- **ምሳሌ 4፣** የቤተሰብ ድንበኞችን የመጠጥ ትዕዛዝ በሚውስዱበት ጊዜ ቤተሰቡ ውስጥ ያለች አንዷት ወጣት ሴት ቢራ አዘዘች። መታወቂያዋን ሲጠይቁ ከ21 አመት በታች መሆኗን ተገነዘቡ። እሷን ለማስተናገድ ፍቃደኛ አይደሉም ነገር ግን ቤተሰቡ ውስጥ ያለች አንዷት ትልቅ ሴት ልጇ እንደሆነች እና ሙሉ ሀላፊነቷን እንደምትወስድ ተናገረች። ያስተናግዷታል?
  - አያስተግዷትም እርስዎ እንደ የፈቃዱ ባለቤት ሙሉ ሀላፊነት አለብዎ።
- **ምሳሌ 5፣** ለንግድ ተቋሜ አዲስ አስተናጋጅ እየቀጠርኩ ነው። ሰራተኛው ምግብ እና የአልኮል መጠጦች የማቅረብ ስራ የሚሰራ ይሆናል። እድሜው 18 የሆነ ወጣት ለስራው አመልክቷል። እሱን መቅጠር እችላለሁ?
  - አዎ! ማስተናገድ ይችላል ፣ ነገር ግን አልኮል መጠጣት አይችልም።

# ክፍት የመጠጥ መያዣዎችን በተመለከት ያሉ ህጎች


- በተሽከርካሪዎች "የተሳፋሪ ቦታዎች" ውስጥ የተከፈቱ የመጠጥ መያዣዎች መኖር የለባቸውም
- የወይን ጠርሙስ ከምግብ ጋር ያዘዙ ደንበኞች ወይኑን ጠጥተው ካልጨረሱ ጠርሙሱን ወደ ቤታቸው ሊወስዱ ይችላሉ።
- ያላለቁ የመጠጥ ጠርሙሶች የንግድ ተቋሙን ለቀው ከመውጣታቸው በፊት በድጋሚ መዘጋት አለባቸው





# ያልተፈቀዱ የአልኮል መጠጦች መገኛዎች

- በእርስዎ የንግድ ተቋም ውስጥ ደንበኞች አልኮል በስጦታ እንዲሰጡዎ መፍቀድ የለብዎትም።
- በፍቃድዎ ስር ከተፈቀዱት በስተቀር ማንኛውንም የአልኮል መጠጦችን ማከማቸት ህገ ወጥ ነው
- ሁሉም የአልኮል መጠጦች ከሞንትጎመሪ የአልኮል እና መጠጦች አገልግሎት (ABS) መጋዘን፣ ከ 27 ቱ መደብሮች ከአንዱ ፣ ወይም ከተፈቀደለት አነስተኛ የወይን ፣ የቢራ  ወይም የመጥመቂያ ፋብሪካ መምጣት አለባቸው።








# የመረጃ ሰነድ አያያዝ

የንግድ ተቋማት የሚከተሉትን በማድረግ ይጠቀማሉ፡-

- የአደጋዎች መዝገብ (የተጠረዘ ደብተር) ፣ መዝገቦችን ለ 3 ዓመታት ጠብቀው ማቆየት አለብዎት
- እንዴት እንደተከሰቱ ለይቶ ማወቅ
- ለአስተዳደር ማሳወቅ
- ከምስክሮችን መረጃ መሰብሰብ እና ሰነዱ ላይ እንዲፈርሙ መጠየቅ


INCIDENT REPORT FORM 001

Information

Date: ____ Time of Day: ____
Manager: ____ Primary Staff Person: ____
Other Staff Involved: ____
Name/Description of Patron: ____

☐ ID Confiscated ☐ Transportation Offered
☐ Non-Alcohol Beverage Served ☐ Police Contacted

Intervention Strategies Used: ____

Witnesses: ____
Comments: ____

Form Completed By: ____
Signature: ____ Date: ____

**የፖሊስ የአደጋ ጊዜ ያልሆነ ስልክ ቁጥር 301-279-8000 ፣ ከአካባቢው ፖሊስ ጋር ጥሩ ግንኙነት ይፍጠሩ**



# ክፍል 5

ኢንስፔክሽኖች

# መደበኛ ኢንስፔክሽኖች


- [x] የአልኮል ፍቃድ በፍሬም ውስጥ በማድረግ እና በቀላሉ ለህዝብ ሊነበብ በሚችል መልኩ ማስቀመጥ
- [x] የአልኮል ግንዛቤ ማረጋገጫ/ በንግድ ተቋሙ በስራ ሰዓት ጊዜ  የአልኮል አገልግሎት ለመስጠት ፍቃድ ያለው ግለሰብ መኖር አለበት
- [ ] በቀላሉ የሚገኙ እና በደንብ የተያዙ ፣ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋለ ስለዚህ በሰፊው እንወያያለን
- [ ] የመጠጥ በርሜል ምዝገባ
- [ ] የመጠጥ ቤት አገልግሎት እና የአሠራር ደንቦች ተግባራዊ ሆነዋል
- [ ] የመገኛ/የማከማቻ ደንቦች ተግባራዊ ሆነዋል።
- [ ] 
- [ ] 

# የአልኮል ፈቃድ

**ጥሩ ምሳሌ**




**መጥፎ ምሳሌ**




- የንግድ ፍቃድ በመስታወት ተሸፍኖ በፍሬም ውስጥ መቀመጥ
- ማህበረሰቡ በቀላሉ ሙሉውን ሰነድ ማንበብ በሚችልበት ቦታ ላይ ይለጠፋል

# የአልኮል ግንዛቤ ስልጠና






- በተፈቀደ የአልኮል ግንዛቤ ፕሮግራም ማረጋገጫ ያለው ግለሰብ አልኮል በሚሸጥባቸው ሰዓታት ውስጥ በንግድ ተቋሙ ውስጥ መገኘት አለበ(ባ)ት

- ይህን ካላከበሩ በንግድ ተቋሙ ላይ ቅጣቶችን ሊያስከትል እና ፈቃድዎን ሊያሳጡ ይችላል

**በአልኮል ግንዛቤ ዙሪያ ሰርተፊኬት ያላቸው ሰራተኞች መኖራቸው የንግድ ተቋሙ የበለጠ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ያደርገዋል**

# መዝገቦች

- የቢራ፣ የወይን እና የአልኮሎች/ሊከሮች ደረሰኞች (ከካውንቲ እና ከግል አቅራቢዎች)
  - በማንኛው ጊዜ በንግድ ተቋሙ ውስጥ መቀመጥ አለበት እናም ቢያንስ ለ 2 ዓመታት ተጠብቆ መቆየት አለበት

- የሰራተኛ መዝገቦች
  - በማንኛው ጊዜ በንግድ ተቋሙ ውስጥ መቀመጥ አለበት እናም ለ 1 ዓመት ተጠብቆ የሚቆይ
  - መዝገቦች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡- ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ወይም ኢሜይል፣ የትውልድ ቀን እና የቅጥር ቀን



ጥሩ ምሳሌ



መጥፎ ምሳሌ

# የመጠጥ በርሜል ምዝገባ






- የእርስዎ ኃላፊነት፡-
  - የትዕዛዝ መመዝገቢያ ደብተር ለማግኘት እንዲችሉ ይህን ቢሮ ያግኙ ፣ የተቆጣጣሪ (Comptroller's) ቢሮ 410-260-6381
  - የመመዝገቢያ ቅጾች ከተሰጡ በኃላ በንግድ ተቋሙ ውስጥ ለ 30 ቀናት ተይዘው መቆየት ይኖርባቸዋል
  - ስቲከሮች መለጠፍ አለባቸው

**ሁሉም የመጠጥ በርሜል ሺያጮች መመዝገብ አለባቸው**

# የባር አሰራሮች



## የአገልግሎት ሰዓቶች




- ከስራ ሰዓት በኋላ የአልኮል ሽያጭ/አገልግሎት አይፈቀድም።
- አልኮል የሚሸጡ ከሆነ ምግብም መሸጥ ይኖርብዎታል።
- በካውንቲው የተቀመጡ የመዝጊያ ሰአቶችን ያክብሩ
  - ቢራ ፣ ወይን እና አልኮል መሸጥ የሚያቆመው ፣
    - ሳምንቱን ሙሉ ከሌሊቱ 2 ኤኤም ፣ ከንግድ ተቋሙ ውጭ ለሚወጡ መጠጦች ሽያጭ ከሌሊቱ 1 ኤኤም ያበቃል
  - ቢራ፣ ወይን እና አልኮል መሸጥ የሚያቆመው ፣
    - ከሌሊቱ 2 ኤኤም ከእሑድ እስከ ሐሙስ
    - ከሌሊቱ 3 ኤኤም አርብ እና ቅዳሜ

## የባር / የጠርሙስ አገልግሎት



- የሚከተሉትን ማድረግ የተከለከለ ነው :-
  - ማንኛውንም ጠርሙስ ወይም መያዣ እንደገና መጠቀም ወይም መሙላት
  - ጠርሙስ ወይም የመጠጥ መያዣ ውስጥ ያሉ መጠጦች መቀየር፣ ማቀላቀል ወይም የአልኮል መጠኑን መጨመር
- ከአልኮል ጋር የሚቀላቀሉ መጠጦች ላይ ቀን መለጠፍ ያስፈልጋል ፣ እነዚህን ከ 5 ቀናት በኋላ መጠቀም አይቻልም
- ጠርሙሶች ኦሪጅናል መለያዎች (labels) ሊለጠፍባቸው ይገባል።
- ከ 21 ዓመት በታች የሆኑ ሰራተኞች አልኮል መሸጥ ይችላሉ (ከ 18 አመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለባቸው)
- ዲስቲልድ (distilled) የሆኑ አልኮሎች የጠርሙስ አገልግሎት አይፈቀድም *በግል ከተከራይ ክፍል ካልሆነ በስተቀር*

# ሌሎች ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች



| | |
|---|---|
| **በአደባባይ መጠጣት**  | ⊘ የሕዝብ የጋራ ቦታዎች ካልተፈቀደ በስተቀር<br>⊘ በአጠቃላይ ለህዝብ ክፍት በሆነ የመኪና ማቆሚያ ቦታ<br>⊘ ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ በቆመ መኪና ውስጥ |
| **እርቃን መሆን እና ወሲባዊ ማሳያዎች**  | • ዝሙት<br>⊘ የወሲብ ድርጊት የሚያሳዩ ምስሎች፣ ቪዲዮዎች ወይም የኤሌክትሮኒክስ ቅጂዎች<br>⊘ የራቁት ዳንስ<br>⊘ ያልተገባ ድርጊት በሚያሳይ ግለሰብ ላይ ዶላር መለጠፍ |
| **ቁማር**  | • ለመጫወት መክፈል (የምግብ/የመጠጥ ግዢን ያካትታል)<br>• የእድል ጨዋታ (a game of chance )<br>• ገንዘብ ወይም ሽልማት ለማግኘት ብቁ መሆን ለተጨማሪ የጨዋታ ጊዜ ቺፕስን (chips) ጨምሮ ሌሎች መክፈል ያለባቸው ፣ ዋጋ ያለው)<br><br>እነዚህን 3 ነገሮች ማካተት አለበት። |

# የአፈጻጸም ክትትል

| | የአፈጻጸም ክትትል |
|---|---|
| "ደንበኛ" | ከ 21 ዓመት በታች |
| የመታወቂያ ማረጋገጫ | ትክክለኛ መታወቂያ (የሀሰት ያልሆነ ወይም ያልተቀየረ መታወቂያ) |
| ዓላማ | ህጎችን ማስከበር |
| ኤጀንሲ | ፖሊስ ፣ የአልኮል እና መጠጦች አገልግሎት (ABS) ኢንስፔክተሮች ፣የስቴት ኢንስፔክተሮች |
| የሚያስከትለው አደጋ | ለንግድ ተቋማት ቅጣቶች ፣ አልኮል ለሚሸጥ/ለሚያስተናግድ ሠራተኛ የወንጀል ክስ |




# ክፍል 6

ከ 21 ዓመት በታች የአልኮል አጠቃቀም እና መታወቂያዎች

# ከ 21 ዓመት በታች የሆኑ ደንበኞችን ማስተናገድ

- **ለንግድ ተቋማት እና ለአስተናጋጆች ጥብቅ ቅጣቶች፡-**
  - ቅጣቶች፣ የእስር ጊዜ እና የአልኮል ፍቃድን መሰረዝ
  - ለመጀመሪያ ወንጀል 1000 ዶላር እና ለተደጋጋሚ ወንጀሎች እስከ $20,000 የሚደርስ ቅጣት
  - የሸጠው ግለሰብ ፣ 2 ዓመት ሊታሰር ይችላል



https://www.youtube.com/watch?v=re5TqWQgWd4



# ተቀባይነት ያላቸው የመታወቂያ አይነቶች



| ተቀባይነት ያለው | ተቀባይነት የሌለው |
|---|---|
| ✓ የሚሰራ የመንጃ ፍቃድ | ⦸ ጊዜው ያለፈበት መታወቂያ |
| ✓ ኤምቪኤ (MVA) ስቴት መታወቂያ | ⦸ የኮሌጅ መታወቂያ |
| ✓ የሚሊተሪ መታወቂያ (Military ID) | ⦸ የውጭ አገር መንጃ ፈቃድ |
| ✓ ቋሚ የመኖሪያ ካርድ / ግሪን ካርድ | ⦸ የክሬዲት ካርድ |
| ✓ የሚሰራ ፓስፖርት ወይም የፓስፖርት ካርድ | ⦸ የቤተ መፃህፍት ካርድ |
| | ⦸ የልደት ምስክር ወረቀት |


# የመታወቂያ መስፈርቶች

- ✓ በመንግስት የተሰጠ
- ✓ የልደት ቀን
- ✓ የባለቤቱ ፎቶ
- ✓ ፊርማ
- ✓ ጊዜው ያላበቃ
- ✓ ያልተበላሸ
- ✓ ኦሪጅናል መታወቂያው መቅረብ አለበት ፤ ፎቶ ተቀባይነት የለውም





# G-R-E-E-T

- **G-** (Get) መታወቂያ በእጅዎ ይቀበሉ
- **R** - (Read) በመታወቂያው ላይ ያለውን መረጃ ያንብቡ
- **E** - (Examine) መታወቂያውን ከሰጥዎት ግለሰብ ጋር ያመሳክሩት
- **E** -(Employ) መታወቂያውን ለማረጋገጥ የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀሙ
- **T** - (Test) ግለሰቡን ለመለየት አንዳንድ ጥያቄዎች ይጠይቁ




# እነዚህን መታወቂያዎች ይለዩ


















# የመታወቂያ አይነቶች













# የመታወቂያ አይነቶች




# የመታወቂያ አይነቶች







## የቁም (Vertical )መታወቂያዎች

ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ነዋሪዎች የሚሰጥ። በቀላሉ መለየት ይቻላል ፣ የሚያበቃበት ቀን በመታወቂያው ላይ ተጽፏል


# መታወቂያው የውሸት፣ ከሌላ ሰው የተወሰደ ወይም የተሰረቀ ነው?

**ምልክቶች**



- ✓ ቁመት/ክብደት/አካላዊ መግለጫው ከግለሰቡ ጋር አይመሳሰልም።
- ✓ አጻጻፍ ግድፈት
- ✓ መቀየሩን የሚያሳዩ ምልክቶች
- ✓ ላምኔት የተደረገ / የተጨማደደ
- ✓ "የዩናይትድ ስቴት የመታወቂያ ካርድ" የሚባል ነገር የለም

**ምን ማድረግ ይቻላል?**



- ✓ ጥንካሬውን ይፈትሹ ፣ መታጠፍ መቻል አለበት
- ✓ ከፍ ያሉ ፊደሎች ፣ ደብዛዛ ምልክቶች እና ሆሎግራሞች (holograms) መኖራቸውን ያስተውሉ
- ✓ የመታወቂያ ማረጋገጫ መመሪያውን እና ሌሎች የአሰራር መንገዶችን ይከተሉ
- ✓ ጥያቄዎችን ይጠይቁ ፣ ቁመት፣ አድራሻ፣ ዚፕ ኮድ ፣ ባለቤቱ ብቻ የሚያውቃቸው መረጃዎች ናቸው
- ✓ 2ኛ መታወቂያ ይጠይቁ
- ✓ ፊርማ ይጠይቁ
- ✓ አሁንም እርግጠኛ ካልሆኑ አገልግሎቱን እንዳይሰጡ
- ✓ መታወቂያውን እንዳይወስዱ

# መታወቂያዎችን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አሰራሮች

- መታወቂያ ማረጋገጫ መመሪያ ፤ የተለያዩ ስቴቶች የተለያዩ መመሪያዎች አላቸው ፤ መመሪያዎቹን ይወቁ
- የመታወቂያ ባርኮድ (Barcode) ማንበቢያዎች
- የእጅ ባትሪዎች እና/ወይም ጥቁር መብራቶች?
- ማጉሊያ መነፅር











# ክፍል 7

የስልጠና ግምገማ እና አንዳንድ ተሳታፊዎችን መሰናበት

# ABS Communication Center

- **ይደውሉ:** 240.777.1900 ፣ ከሰኞ እስከ አርብ  ከ 8:00 ኤኤም  እስከ 4:30 ፒኤም
- **ኢሜይል፡-** ABS@montgomerycountymd.gov
- **ያግኙን** ፣ ከአልኮል እና መጠጦች አገልግሎት (ABS)  ባለሙያዎች ጋር፣ የሁለትዮሽ የግንኙነት መንገድ
- **ንቁ አገልግሎት** ፣ በትዕዛዝ ሁኔታ እና የእቃ አቅርቦት ጉዳይ ዙሪያ
- **የሚለካ ምላሽ ሰጪነት** ፣ ለጥያቄዎችዎ
- **አይስቶር (iStore)፣** የእርስዎን አይስቶር (iStore) አካውንትን በተመለከተ ለማንኛውም ጥያቄዎች የአልኮል እና መጠጦች አገልግሎት (ABS) ባለሙያዎች ጋር ይገናኙ

**የአልኮል እና መጠጦች አገልግሎት (ABS) የኮምኒኬሽን ማዕከል**

**እኛ እርስዎን ለማገልገል ዝግጅ ነን!**

ALCOHOL BEVERAGE SERVICES

# እናመሰግናለን!

## የፈቃድ ሰጪ ፣ የደንብ እና የትምህርት ክፍል

| የፍቃድ ሰጪ ሃላፊ | 240.777.1989 |
| --- | --- |
| የአፈጻጸም ክትትል ኃላፊ | 240.777.1999 |
| ቅድመ-ፍቃድ አሰጣጥ | 240.777.1936 |
| የማህበረሰብ ስራዎች | 240.777.1999 |

# በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ይከታተሉን



Facebook:
@MoCoRASP

X:
@MoCo_RASP

Instagram:
@MoCoRASP

# ክፍል 8

## የፍቃድ ኮሚሽነሮች ቦርድ (BLC)
## ችሎቶች አሰራር ላይ ስልጠና




# የፍቃድ ኮሚሽነሮች ቦርድ ማን ነው?



- የአልኮል እና መጠጦች አገልግሎት (ABS) / የፈቃድ ፣ የደንብ እና የትምህርት ክፍል (LRE) ሰራተኞች በካውንቲው ስራ አስፈፃሚ የተሾመውን የፍቃድ ኮሚሽነሮች ቦርድ (የአልኮል ቦርድ) ይደግፋሉ።
- አዲስ ፈቃዶችን ያጸድቃል፣ ፈቃዶችን ያስተላልፋል እንዲሁም የአንድ ቀን ፈቃዶችን ያጸድቃል
- ማንኛውም ለውጦች (የንግድ ተቋሙ የቤት ውስጥ አቀማመጥ ፣ ምን ያህል ሰው በአንድ ጊዜ እንደሚያስተናግድ እና የስራ ሰዓትን ጨምሮ) ለፈቃድ ሰጪው ቢሮ መቅረብ አለባቸው። ማንኛውንም ለውጦች ለማሳወቅ ለፍቃድ ሰጪው ቢሮ በጽሁፍ ያሳውቁ
- ዓመታዊ እድሳት
- የችሎቶች ውሳኔ አለማክበር / ጥሰቶች
- እስከ $20,000 የሚደርስ ቅጣት ፣ ፈቃዶችን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል።

***አስፈላጊ፣ ፈቃዱ ከተሰረዘ በኃላ የፈቃዱ ባለቤት በሜሪላንድ ውስጥ የአልኮል መጠጥ ፈቃድ ሊኖረው አይችልም?***

ፎቶው የተወሰደው ፣ Bethesda Magazine

# ለችሎቱ የሚደረግ ዝግጅት

- ሁሉም አመልካቾች እና አስተዳዳሪዎች በችሎቱ ላይ መገኘት አለባቸው
- ችሎት የሚካሄደው 201 Edison Park Dr. Gaithersburg, MD በሚገኘው ቢሮአችን ነው።
- የንግዱን አይነት፣ የንግዱን ጽንሰ ሃሳብ እና ንግዱ የሚለይበትን መንገድ ባጭሩ ያብራሩ
- ስለ ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ለመናገር ዝግጁ ይሁኑ፡-
  - በምንትጎመሪ ካውንቲ (የምግብ እና/ወይም የአልኮል አገልግሎት ፣ የአልኮል መጠጥ ማስተናገድ ፣ ተቋምን ማስተዳደር፣ የንግድ ሥራ ባለቤት መሆን፣ ወዘተ) **ልምድ ሊኖርዎት ይችላል** ።
  - አሁን ያሉ **ጥሰቶች**



# ለችሎትዎ የሚያደርጉት ዝግጅት

**የሚከተለውን እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ፡-**

- ከችሎቱ በፊት ንግድ ተቋሙን የውስጥ አቀማመጥ ማለትም መግቢያዎችን፣ የተናጠል መቀመጫዎችን፣ የእቃ ማስቀመጫዎችን ፣ መታጠቢያ ቤቶችን፣ ማብሰያ ክፍሎችን፣ ባርን፣ የውጪ ካፌዎችን፣ መውጫዎችን እና ግድግዳዎችን ጨምሮ ስካን (scan) በማድረግ በኢሜል እንዲልኩ
- የንግድ ተቋሙን የውስጥ አቀማመጥ (floor plan) በአጭሩ እንዲያብራሩ
- ምግብ የሚሸጡ ከሆነ የምግብ ዝርዝር (ሜኑ) ኮፒ እንዲያስገቡ
- ከችሎት ቀንዎ በፊት በዙም (Zoom) መታወቂያ የመለየት ፈተና እንዲወስዱ። 10 መታወቂያዎችን ትክክለኛነት ይለያሉ።



# የማረጋገጫ ጥያቄዎች

- አንድ ሰው አልኮል **ለመግዛት ዕድሜው ስንት** መሆን አለበት?

  21_አመት

- አንድ ሰው በሚሪላንድ ውስጥ አልኮል **ለመሸጥ ስንት ዓመት** መሆን አለበት?

  18 አመት

- ተቀባይነት ያላቸው **5 የመታወቂያ ዓይነቶች** የትኞቹ ናቸው?
  - በስቴት የተሰጠ የመንጃ ፍቃድ
  - በስቴት የተሰጠ (MVA) መታወቂያ ካርድ
  - ፓስፖርት
  - የሚሊተሪ መታወቂያ (Military ID)
  - የኢሚግሬሽን ካርድ/ ግሪን ካርድ



# የማረጋገጫ ጥያቄዎች



- **የሰራተኛ መዝገቦች እና ሁሉም የአልኮል ደረሰኞች፡-**
  - <u>የሰራተኛዎን መዝገቦች እና የአልኮል ኢንቮይሶችን/ደረሰኞችን የት ማስቀመጥ አለብዎት ?</u>

    *በንግድ ተቋሙ ውስጥ ተቆጣጣሪ ወይም ፖሊስ በማንኛውም ጊዜ ሊያገኙት እንዲችሉ ሳይቆለፍ መቀመጥ አለበት ፤።*
  - <u>ከስራ የለቀቁ ሰራተኞች መዝገቦችን ለምን ያህል ጊዜ ይዘው ማቆየት ይኖርብዎታል?</u>

    *ከለቀቁ በኃላ እስከ አንድ አመት ድረስ ፣ አሁን ያሉ ሰራተኞች መዝገቦች በንግድ ተቋሙ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ መገኘት ይኖርባቸዋል*
  - <u>የአልኮሆል ኢንቮይሶችን/ደረሰኞችን ለምን ያህል ጊዜ መያዝ አለብዎ?</u>

    *ሁለት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ*
- **አልኮል መግዛት ፤**
  - <u>የአልኮል መጠጥ ከየት መግዛት ይኖርብዎታል?</u>

    *የምንትጎመሪ ካውንቲ የአልኮል መጠጥ አገልግሎት፣ ከምንትጎመሪ ካውንቲ የአልኮል መሸጫ መደብሮች ውስጥ ከአንዱ፣ ወይም ከተፈቀደላቸው አነስተኛ የወይን ፤ የቢራ ፋብሪካዎች ወይም ጠማቂዎች*



# የማረጋገጫ ጥያቄዎች



- ለክላስ (Class) B ፍቃድ ብቻ (ቢራ፣ ወይን እና አልኮል) ከፍተኛው ህጋዊ የምግብ እና የአልኮል ሬሾ (ratio) መስፈርት ምን ያህል ነው? ምን ያህል ሬሾ (ratio) እንዲኖርዎት ይጠበቃል?

  60% አልኮል / 40% ምግብ ፣ (60/40) የምግብ ሽያጩ ከፍ ባለ መጠን የተሻለ ይሆናል።

- የአልኮል ሕግ አፈጻጸም እና ቁጥጥር ስልጠና (ALERT) ውስጥ ተሳትፈዋል? የአልኮል ሕግ አፈጻጸም እና ቁጥጥር ስልጠና (ALERT) ውስጥ የሚሳተፉ ምን ያህል ሰራተኞች ይኖርዎታል?

  ሁሉንም ወይም አብዛኛውን ሰራተኞችን ማሰልጠን በጣም ጠቃሚ ተግባር ነው። ?

- ምን ያህል ሰራተኞች ይኖሩዎታል? ምን ያህሉ የአልኮል ግንዛቤ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይኖራቸዋል?
  - ሁሉንም ወይም አብዛኛውን ሰራተኞችን ማሰልጠን በጣም ጠቃሚ ተግባር ነው።
  - ሰርተፊኬት ያለው ግለሰብ በማንኛውም የስራ ጊዜ በንግድ ተቋሙ ውስጥ መሆን አለበት።


- በንግድዎ አካባቢ ስላሉት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያውቃሉ?



# የማረጋገጫ ጥያቄዎች



- ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ዝግጁ ይሁኑ።
  - <u>የዕለት ተዕለት መደበኛ የስራ ሰዓቶችን ይዘርዝሩ (እነዚህ ሊለወጡ ይችላሉ )</u>
  - <u>ምን ምን የአልኮል መጠጥ ሽያጭ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች አልዎት?</u>
  - <u>ለሰራተኞችዎ በአልኮል ዙሪያ በጽሁፍ የተዘጋጁ ፖሊሲዎች አልዎት</u> ?
  - <u>ፕሮሞተር (promoter) ይጠቀማሉ?</u>
  - <u>የቁም (vertical) መታወቂያዎችን ይቀበላሉ?</u>




የቁም (Vertical) = ከ 21 በታች




አግድም (Horizontal) = ከ 21 በላይ



# የመጠጥ ቦርድ ችሎት ፤ እያጠናቀቅን ነው

- ደብዳቤ እና የውሳኔው ኮፒ በ 10 ቀናት ውስጥ በኢሜል ይደርሰዎታል?
- ከችሎቱ በኋላ፣ የአልኮል ፍቃድዎን ለመውሰድ እንዲችሉ እና የመጨረሻ ኢንስፔክሽን ለማድረግ ወደ ፍቃድ ሰጪው ቢሮ በ 240.777.1999 ይደውሉ።
- ለመጨረሻው ኢንስፔክሽን የሚከተሉትን ማቅረብ ያስፈልግዎታል
  - *የአጠቃቀም እና በባለቤትነት የመያዣ ሰርተፊኬት*
  - *የምግብ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ፈቃድ*
  - *የአልኮል ሰርተፊኬት*
  - *የሜሪላንድ የሽያጭ እና የአጠቃቀም ታክስ ፍቃድ*
  - *የነጋዴዎች ፍቃድ*
  - *የጅምላ ማስተላለፍ ፈቃድ (ለማስተላለፊያ ማመልከቻዎች)*



# ዓመታዊ የንግድ ፍቃድ እድሳት

- በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ አልኮል የመሸጥ/የማስተናገድ ሁሉም ፈቃዶች **በየአመቱ በሜይ 1 12፡00 ኤኤም ላይ ያበቃሉ**
- ማመልከቻዎች እስከ ማርች 31 ድረስ መግባት ወይም ፖስትማርክ (postmarked) መደረግ አለባቸው። የአልኮል እና መጠጦች አገልግሎት (ABS) ይህን ድህረ-ገጽ በመጠቀም ማመልከቻዎን በኦላይን እንዲያስገቡ ይመከራል ፤ https://www.montgomerycountymd.gov/ABS/licensure/license/
- በዓመት **ሁለት** ክፍያዎች ይከፈላሉ፡-
  - ፍቃድ ለማደስ ማመልከቻ በሚያስገቡበት ጊዜ የ 100 ዶላር ክፍያ ይከፍላሉ
  - ፈቃዱን በሚወስዱበት ጊዜ የሚከፈለው የፍቃድ ክፍያ (እንደ ፍቃዱ አይነት ይለያያል)



# ከማጠናቀቃችን በፊት....

- ፈቃድዎን ለማስተላለፍ ውሳኔው ከደረሰዎት 30 ቀናት እና አዲሱን ፈቃድ ለመውሰድ 2 ዓመታት አልዎት
- የንግድ ግዢ ከተፈጸመ በኃላ የዝውውር ማመልከቻ ለማስገባት 30 ቀናት አልዎት

- ለተከታታይ 10 ቀናት ከዘጉ የፈቃዱ ማብቂያ ጊዜ የ 10 ቀን ማሳወቅያ ሳያገኙ እንዳይቀሩ ለቦርዱ በጽሁፍ ወይም በኢሜል ማሳወቅ አለብዎት።
- ጥያቄዎች አሉ?



ALCOHOL BEVERAGE SERVICES

# የፈቃድ ፣ የደንብ እና የትምህርት ክፍል

# እናመሰግናለን!

| የፍቃድ ሰጪ ሃላፊ | 240.777.1989 |
| --- | --- |
| የአፈጻጸም ክትትል ኃላፊ | 240.777.1999 |
| ቅድመ-ፍቃድ አሰጣጥ | 240.777.1936 |
| የማህበረሰብ ስራዎች | 240.777.1999 |

በ Facebook @MoCoRASP ወይም Twitter @ MoCo_RASP ላይ ይከተሉን።
Instagram @mocorasp